# Ethio-Cologne Sport und Kultur (ECSK) e.V
# ኢትዮ ኮለን የስፖርትና የባህል ማህበር (ኢኮስባማ)

Ethio-Cologne Sport und Kultur e.V. Postfach 800 234 51002 Köln Germany

Ethio-Cologne Sport und. Kultur e.V.
c/o Tesfaye Manayehu-Abebe
Vorstandsvorsitzender
Postfach 26 01 80
50514 Köln

0049 (0) 151 55033101
Info_ethiocologne@yahoo.com

Vereinsregisternummer: VR 14531
Steuernummer: 223/5905/0781
Finanzamt: Köln-West

**Köln, 29.04.2015**

ዛሬ ይህንን የምስጋና መልዕክት በኢትዮ ኰሎኝ ስፖርትና የባህል ማህበር ስም ስናስተላልፍ ጥልቅ ስሜት ዉስጥ ሆነን ነዉ። የዛሬ ሳምንት 25.04.15 በኰሎኝና በአካባቢው የምንገኝ ህብረተሰብ በሊቢያ በሳዉዝ አፍሪካ እንዲሁም በየመን የሚገኙ ወገኖቻችን ላይ የደረሰዉን አሰቃቂ ግድያ በደልና ስቃይ ለማሰብና ለመዘከር በመገናኘታችን ሁላችንም የህሊና ዕረፍት ያገኘን ይመስለናል። ምንም እንኳን ለተሰዉትና በስቃይ ለሚገኙት ወገኖቻችን ከፀሎትና ፈጣሪን ከመለመን ያለፈ የምናደርግላቸዉ አቅምና ጉልበት ባይኖረንም ለመንግስትም ይሁን ለተለያዩ ተቋሞች እንዲሁም ለእያንዳንዳችን ትልቅ የቤት ስራ ነዉ የሰጡን ይህንን የቤት ስራ እንዴት እንደምንወጣዉ ቆም ብለን ልናስብ ይገባናል።

አሁንም አጥብቀን የምንጠይቀዉ በኃይማኖት በጎሳ በዘረኝነት በጠባብ አመለካከት መከፋፈሉን ወደ ጐን ትተን ኢትዮጵያ ኢትዮጵያ ዕያልን የምንዘምርላት አገራችን ከተጠነሰሰላት ከባድ አደጋ እኛዉ ለኛዉ መፍትሄ ለማምጣት በግልፅና በቅንነት በመነሳት ዛሬውኑ ከዚህ ቅርብ ካለነው መጀመር እንዳለብን ይሰማናል። ጥሪያችንን አክብራችሁ የወንድሞቻችንን ደምና ስቃይ በህብረት ለማሰብ በመገናኘታችን ከልብ እናመሰግናለን ህብረታችንን በማጠንከር ታሪካችንን ለመቀየር ዛሬ ነገ ሳንል መነሳት ይኖርብናል።



በመጀመሪያ ሁላችሁም እንደዚህ ተሰባስበን የወገኖቻችንን ሀዘን ደምና ስቃይ ለማሰብ በመገናኘታችን በፈጣሪ ስም ላመሰገን እወዳለሁ::
እኛ ዛሬ በዚህ ሰዓት እንዲህ ለመገናኘት የበቃነዉ ያለንበት አገር ወይም ቦታ ሰላም በመሆኑ ነዉ::
የዚህችን ዓለም ሰላም ለማፍረስ በኃይማኖት ስም በጠባብ ዘረኝነት ላይ የተመሰረተ ዘመቻ በየቦታዉ እይተስፋፋ ይገኛል እውነት ይህች አለም ለስዉ ልጆች ጠባብ ነዉን?
ይህንን ክፋትና በሰዉ ልጆች ደምና ስቃይ ?? ማድረግን የሚፈቅድ የሚያስተምር የሚያስተባብር የሚያደራጅ ሀይማኖት ወይም የእምነት ተቋም በየትኛዉም የሀይማኖት መፅሀፍ እንደማይገኝ እርግጠኛ ነኝ ግን የተወሰኑ ግለሰቦች ብዱኖች የሚያራምዱት ሰይጣናዊ ተግባር ነዉ ማለት ይቀላል:: ይህንን አረመናዊ ዘመቻ ለማቆም ሁሉም የየራሱን ድርሻ ሊወጣ ይገባል::
እኛ ኢትዮጵያዉያን: ኢርትራዊያን: በጠቅላላው አፍርካዊያን ከየትኛዉም ዓለም የተሻለ ዕምቅ የተፈጥሮ ሀብትና የህዝብ ብዛት እንዲሁም አምቺ መልካ ምዕድራዊ አቀማመጥ ያለን ህዝቦች ብንሆንም ለስደት ለርሃብ ለበሽታና ለእርስ በእርስ ጦርነት የተጋለጥነዉ እኛ ነን ግን ለምን? ይህን ጥያቄ ሁላችንም እራሳችንን እንጠይቅ::
ዘረኝነት አክራሪነትን ጠባብ አመለካከትን መከፋፈልን ወደ ጎን ትተን በየበራሃዉ በየባህሩ በሽታና እኔ እብለጥ እኔ በማለት እርስ በእርስ የሚተላለቀዉን ወገኖቻችንን በዚህ ይብቃ የምንልበትና ከተነሱብን አሸባሪዎች ነፃ የምንወጣበት ወሳኝ ሰዓት ላይ ነን::
አሁንም እንደ ሰማዕት የፈሰሰዉን የወንድሞቻችን ደም ፈጣሪ ይስብለን ነፍሳቸዉንም በገነት ያኖራት ዘንድ ወዳንተ እንማልዳለን:: የተቀሩትን በስጋትና በስቃይ ላይ የሚገኙትን ወገኖቻችንን ከሰውም ይሁን ከፈጣሪ መፍተሄ እንዲያገኙ ተግተን እንድንጸልይ በትህትና እጠይቃለሁ::
ኢትዮጵያን ቀሪዉንም አለም ፈጣሪ ይጠብቅልንን::
የኢትዮ-ኮለኝ ስፖርትና የባህል ማህበር አባላት ደጋፊዎች እና የኮለን ነዋሪዎች በስደት በሚገኙ ኢትዮጵያዉያን ወገኖቻችን ላይ በደቡብ አፍሪካ: በየመን እና በሊቢያ በደረሰዉ አስቃቂ ግድያ እና ሰብአዊነት የጎደልዉ ድርጊት ልባችን የተሰበረ መሆኑን እንገለጻለን: ለሟች ቤተሰቦች እና ለመላዉ የኢትዮጵያ ሕዝብ በአገር ዉስጥም በውጭም መጽናናትን እንመኛለን::



# Ethio-Cologne Sport und Kultur (ECSK) e.V
# ኢትዮ ኮለን የስፖርትና የባህል ማህበር (ኢኮስባማ)

Ethio-Cologne Sport und Kultur e.V. Postfach 800 234 51002 Köln Germany



# Ethio-Cologne Sport und Kultur (ECSK) e.V
# ኢትዮ ኮለን የስፖርትና የባህል ማህበር (ኢኮስባማ)

Ethio-Cologne Sport und Kultur e.V. Postfach 800 234 51002 Köln Germany





# Ethio-Cologne Sport und Kultur (ECSK) e.V
# ኢትዮ ኮለን የስፖርትና የባህል ማህበር (ኢኮስባማ)

Ethio-Cologne Sport und Kultur e.V. Postfach 800 234 51002 Köln Germany





**Ethio-Cologne Sport und Kultur e.V.**
Postfach 26 01 80
**50514 Köln**

**www.ethiocologne.com**
info_ethiocologne@yahoo..com
**Tel:** 0049 (0) 151 55033101

**Bankverbindung**
Sparkasse KölnBonn
Ko.Nr. : 1931388985
BLZ: 37050198

**Registergericht**
Amtsgericht Köln
VR-Nr.: 14531

**Finanzamt:**
Köln-West
StNr:223/5905/0781

# Ethio-Cologne Sport und Kultur (ECSK) e.V
# ኢትዮ ኮለን የስፓርትና የባህል ማህበር (ኢኮስባማ)

Ethio-Cologne Sport und Kultur e.V. Postfach 800 234 51002 Köln Germany





# Ethio-Cologne Sport und Kultur (ECSK) e.V
# ኢትዮ ኮለን የስፖርትና የባህል ማህበር (ኢኮስባማ)

Ethio-Cologne Sport und Kultur e.V. Postfach 800 234 51002 Köln Germany





ከሰላምታ ጋር
ሕብረት ሓይል ነዉ!!
ኢትዮ-ኮለን የስፖርት እና የባህል ማህበር